# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

## ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) የአመራር ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ

ሚያዝያ 12 ቀን 2000 ዓ. ም
April 20, 2008

የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አመራር ምክር ቤት ለሦስት ቀናት ከሚያዚያ 9 እስከ 11፣ 2000 ዓ.ም 2ኛ ሙሉ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል። ስብሰባዉ ሰፋ ያለ አገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮችን በጥልቀት መርምሮ ተገቢና አስፈላጊ ዉሳኔዎችን አስተላልፏል።

አሳሳቢና በጣም አስጊ እየሆኑ የመጡትን የኢትዮጵያ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ከመመባባስ ለመግታትና ለመለወጥ በሚያስችሉት መንገዶች ላይ ሰፊ ውይይት አድርጓል። አገሪቱንና ሕዝቡን ከጥፋት ለማዳን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በሙሉ ሊያስሚሚችው በሚችሉ ዋና ዋና የሀገራችንና የህዝባችን የጋራ ጉዳዮች ላይ እንዲተባበሩና በጋራ እንዲታገሉ ሀገራዊ ጥሪ አቅርቦላቸዋል። ኢሕአፓ(ዴ) በዚህ የኅብረትና የጋራ ትግል ላይ ያለውን ጠንካራ እምነት መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ብሄራዊ ሉዓላዊነት እንዲሁም የሕዝባችንን መሠረታዊ መብቶች (ሰብዓዊ፡ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ) መከበር አቋማቸው ካደረጉ ኢትዮጵያዊ የተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ጋር ለመተባበርና ለመተጋገዝ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል።

በህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ እየተስፋፋ ያለው መርዛማ የዘርና የጎሳ ፖለቲካ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ እየፈጠረው ያለውን ሀገራዊና አካባቢአዊ አደጋዎችን አስፈላጊ የሆኑ የትግል ስልቶችን በመጠቀም ለመመከትና ለመከላከል ኢሕአፓ(ዴ) አሁንም ዝግጁነቱን ያረጋግጣል። ይህንን ሀገራችንና ሕዝባችንን ለጥፋት የዳረገ የህወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ ሥርዓት ለመቀየር የሚደረገው ትግል በሀገሪቱና በሕዝቡ ላይ እስከዛሬ ከደረሱትና ከታዩትም የከፉና የባሱ ጉዳቶችና መዘዞች ለማዳን ሃላፊነት በተሞላው መንገድ ኃይል አቅናጅቶ ለመታገል ቃል ገብቷል። ይህንንም ለማድረግ የሚያስችሉትን ውስጣዊ ድርጅታዊ መስተካከሎችን አድርጓል። በተዋረድ ላሉት የድርጅቱ አካላትም የተግባር መመሪያዎችን ሰጥቷል።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤

ሀገሪቱንና ሕዝቡን ከተቃጣባቸው አደጋዎች የማዳን ትግሉና ሃላፊነቱ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ኢሕአፓ(ዴ) ያምናል። ኢሕአፓ(ዴ) የተለመደውን ኢሕአፓዊ ቁርጠኛነቱንና ዝግጁነቱን እያረጋገጠ ራሱን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስተማማኝ የትግል መሣሪያነት ያቀርባል። ለኢትዮጵያ

ሕዝብ ፍላጎት እራሱን ተገዢ ለማድረግ የገባውን ቃልኪዳን እንደገና ያድሳል። በአንጻሩም ኢሕአፓ(ዴ) መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የትግሉ ሙሉ ባለቤትነቱን አውቆና ተገንዝቦ እንዲተባበረውም ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ትግሉ ድል ይቀዳጃል!

850 Sligo Avenue Suite # 8
Siver Spring , MD 20910

P.O.Box 8141
Silver Spring, MD 20910

P.O.Box 88675
Los Angeles, CA 90009

Fax: 202-449-8363
Email Address: E Mail To EPRP@ AOL.Com